ፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
FEDERAL SUPREME COURT

ቀን/Date 07 ሰኔ 2014

ቁጥር/ Ref. No. [illegible]-30/3802

ለፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት

ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት

<u>አዲስ አበባ</u>

ጉዳዩ፡- **<u>የፌደራል ፍርድ ቤቶች የችሎት ስርዓት መመሪያ የፀደቀ መሆኑን ስለማሳወቅ</u>**

ከላይ በርእሱ ለመጥቀስ እንደተሞከረዉ በፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የፌደራል ፍርድ ቤቶች የችሎት ስርዓት መመሪያን አፅድቋል፡፡

በመሆኑም የፌደራል ፍርድ ቤቶች የችሎት ስርዓት መመሪያ ቁጥር 13/2014 ሥራ ላይ እንዲዉል እንዲደረግ እያሳሰብኩ የፀደቀዉን መመሪያ የያዘ 18 ገፅ ከዚህ ሸኚ ደብዳቤ ጋር አያይዘን የላክን መሆኑን አሳውቃለሁ፡፡

ከሠላምታ ጋር

ሰለሞን አረዳ ዋቅ...
የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት
ም/ፕሬዚዳንት

Federal Supreme Court The Federal Democritic Republe of Etiopian

<u>ግልባጭ</u>

- ለክብርት ፕሬዝዳንት ጽ/ቤት
- ለክቡር ምክትል ፕሬዝዳንት ጽ/ቤት
- ለኮርት ማናጀር ጽ/ቤት

<u>ፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት</u>

ፌ/ከ/ፍ/ቤት
መዝገብ ቤት

ደብዳቤው የደረሰበት ቀን 07/10/14
የተመራበት ቀን 07/10/14
ከፋይሉ ጋር የተያያዘበት ቀን
የገቢ ፕሮቶኮል ቁጥር 6050
የማህደር ቁጥር 38
የተመለሰበት ቀን

ስልክ/Tel. +251 111 553400
ፋክስ/Fax +251 111 550278
ፖ.ሳ.ቁ/P.O.Box 6166
www.fsc.gov.et

የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

# የፌደራል ፍርድ ቤቶች የችሎት
# ስርዓት መመሪያ ቁጥር
# 13/2014

ግንቦት 2014 ዓ.ም

የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

# የፌደራል ፍርድ ቤቶች የችሎት ስርዓት መመሪያ ቁጥር 13/2014

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገመንግስት የዳኝነት ስልጣን ለፍርድ ቤቶች የተሰጠ ከፍተኛ ኃላፊነት በመሆኑ ይህንን ኃላፊነት ከፍተኛ ስነ ምግባር የተላበሰ ተቋማዊ ባህልን መገንባት እና መተግበር በማስፈለጉ፣ በፍርድ ቤቶች እስካሁን የችሎት ስርዓት መመሪያ ባለመኖሩ፣ ወጥነት እና ግልጽነት የጎደለው የችሎት ስርዓት አሰራር መከተል አለመቻሉን ከግምት በማስገባት፣

ፍርድ ቤቶች የችሎትን ስርዓት በሚጥሱ የፍ/ቤት ተገልጋዮች ላይ በዳኞች የሚሰጠው ቅጣት ወጥነት ያልነበረው በመሆኑ ወጥነት እና ተገማችነት እንዲኖረው ማድረጉ አስፈላጊ በመሆኑ፣

ዳኞች፣ ተከራካሪ ወገኖች፣ ተገልጋዮች፣ የችሎት ታዳሚዎች የፍርድ ቤቱ ማህበረሰብ እንዲሁም ሌሎችም የችሎት ሥርዓት እና አካሄድ እንዲያውቁ፣ እንዲያከብሩ፣ እንዲያስከብሩ እና እንዲመሩበት ማድረግ አስፈላጊ በመሆኑ፣ የችሎት ስርዓት በማክበር እና በማስከበር የህብረተሰቡን በፍርድ ቤት ላይ ያለውን አመኔታ ለማረጋገጥ፣

በፌደራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀፅ 55(2) መሰረት የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይህን የፌደራል ፍርድ ቤቶች የችሎት ስርዓት መመሪያ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

### 1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ «የፌደራል ፍርድ ቤቶች የችሎት ስርዓት መመሪያ ቁጥር 13/2014» ተብሎ ሊጠራ ይችላል፡፡

### 2. ትርጓሜ

የቃሉ አግባብ ሌላ ትርጉም ካላሰጠው በስተቀር በዚህ የፌደራል ፍርድ ቤቶች የችሎት ስርዓት መመሪያ ውስጥ፡-

1. «ፍርድ ቤት» ማለት በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ-መንግስት እና በፌደራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 መሰረት የተቋቋመ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት፣ የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት እና የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ማለት ነው፡፡
2. «ጉባኤ» ማለት በፌደራል ዳኝነት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 1233/2013 አንቀፅ 5 መሰረት የተቋቋመ የፌደራል የዳኞች አስተዳደር ጉባዔ ማለት ነው፡፡

3. «የፍርድ ቤት አመራር» ማለት የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት፣ የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት እና የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንቶችና ምክትል ፕሬዚዳንቶች ማለት ነው፡፡

4. «ዳኛ» ማለት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የተሾመ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት፣ የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት እና የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ዳኛ ማለት ሲሆን ጊዜያዊ ዳኛንም ይጨምራል፡፡

5. «የጉባኤ ተሿሚዎች» ማለት በፌደራል የዳኝነት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 1233/2013 መሰረት በዳኞች አስተዳደር ጉባኤ የሚሾም ሰው ማለት ነው፡፡

6. «አስተዳደር ሠራተኛ» ማለት በፌደራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ እንዲሁም በሌሎች ሕጎች መሰረት የሚተዳደር ማንኛውም ሰራተኛ ማለት ነው፡፡

7. «ችሎት» ማለት ዳኛ ወይም ዳኞች ጉዳዮችን የሚያከራክሩበት፣ ምስክሮች የሚሰሙበት ፣ የዳኝነት አገልግሎቶች የሚሰጡበት እንዲሁም ውሳኔ የሚያነቡበት የችሎት ማስቻያ ቦታ፣ ስፍራ ወይም የዳኞች ፅህፈት ቤት ማለት ነው፡፡

8. «የችሎት ፖሊስ» ማለት የችሎት ስርዓት እንዲያስከብር ከሚመለከተው የፌደራል ወይም የአዲስ አበባ ወይም የድሬደዋ ከተማ አስተዳደር የፖሊስ ተቋም የተመደበ ፖሊስ ወይም በክልል ማስቻያ ስፍራዎች ከክልሉ ፖሊስ ተቋም የሚመደብ ወይም በፍርድ ቤቱ በፖሊስነት የሚቀጠር ሰው ማለት ነው፡፡

9. «የችሎት ስርዓት አስከባሪ» ማለት በፍርድ ቤቱ የሚተዳደር የችሎት ስርዓት የሚያስከብር ሰራተኛ ማለት ነው፡፡

10. «አቃቤ ህግ» ማለት በፌደራል ፍትሕ ሚኒስቴር ማቋቋሚያ ህጎች መሰረት አቃቤ ህግ ተብሎ የተሾመ ሲሆን የክልል ዐቃብያነ ህግንም ሆነ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፍትህ ቢሮ የተሾመ ዐቃብያነ ህግን ይጨምራል፡፡

11. «ጠበቃ» ማለት የጥብቅና ሙያ አገልግሎት ለመስጠት ስልጣን ካለው አካል ፈቃድ ያገኘ የህግ ባለሙያ ሲሆን እንደ አስፈላጊነቱ የጥብቅና ፈቃድም ሳይኖረው የግል ድርጅቶች፣ የልማት ድርጅቶች እንዲሁም ሌሎች የመንግስት መስሪያ ቤቶችን ወክሎ የሚከራከር ነገረፈጅ ሆኖ የመከላከያና የፌደራል ፖሊስ ነገረፈጅ እንዲሁም ተከላካይ ጠበቆችንም ይጨምራል፡፡

Federal Supreme Court The Federal Democrtic Repubile of Ethiopia

12. «አስተርጓሚ» ማለት የሀገር ውስጥ፣ የውጪ ቋንቋ፣ የምልክት ቋንቋ በብቃት መስማትና መናገር የሚችልና የፌደራል መንግስት የስራ ቋንቋ የሚችል ሆኖ ይህን የማስተርጎም አገልግሎት የሚሰጥ ሰው ማለት ነው።

13. «ባለ ጉዳዮች» ማለት እየተካሄደ ባለ ክርክር ውስጥ የሚሳተፉ እንደ ከሳሽ፣ ተከሳሽ፣ አመልካች፣ዐቃቢያነህግ፣ ጠበቃ፣አቤቱታ አቅራቢ፣ ተጠሪ፣ የክርክር ጣልቃ ገቦች፣ ውሳኔ ለመቃወም ወደ ክርክር የገቡ ወይም የይግባኝ ባይ እና የመልስ ሰጪ ሆነው ችሎት ላይ የቀረቡ ወይም ማንኛውም የፍርድ ቤቱ ተገልጋይ ማለት ነው።

14. «ምስክር» ማለት በክስ ወይም መልስ ላይ የተዘረዘረ ወይም በፍርድ ቤት ትዕዛዝ ችሎት ላይ ቀርቦ የምስክርነት ቃሉን የሚሰጥ ምስክር ማለት ሲሆን የባለሙያ ምስክርን ይጨምራል።

15. «ፖሊስ» ማለት የፍርድ ቤትን ትዕዛዝ ለመፈጸም ችሎት ላይ የሚቀርብ ፖሊስ ሲሆን የማረሚያ ቤት ፖሊስ፣ የክልል ፖሊስ፣ ፌደራል ፖሊስ፣የጉምሩክ መስሪያ ቤት ፖሊስ እና ትራፊክ ፖሊስን ይጨምራል።

3. የጾታ አገላለፅ

በዚህ መመሪያ ማንኛውም በወንድ ጾታ የተገለፀው አነጋገር የሴት ፆታንም ያካትታል።

4. የተፈጻሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ በፌደራል ፍርድ ቤቶች ችሎት ሂደት ሁሉ ላይ በችሎት ሂደት ውስጥ በሚሳተፍ ማንኛውም ሰው በተለይ ዳኛ፣ የጉባኤ ተሿሚዎች፣ ተከራካሪዎች፣ ምስክሮች፣ አስተርጓሚ፣ የፍርድ ቤቱ አስተዳደር ሰራተኞች፣ የችሎት ስነ ስርዓት አስከባሪ ፖሊሶች፣ የፍርድ ቤቱ ችሎት ስነ ስርዓት ሰራተኞች፣ የችሎት ታዳሚዎች፣ ፖሊሶች፣ ዓቃቢያነ ህግ፣ ጠበቆች ወይም ከችሎት ውጪ በፍርድ ቤቱ ቅጥር ግቢ በሚገኝ ማንኛውም ሰው ላይ ተፈጻሚነት ይኖረዋል።

## ክፍል ሁለት

## የፌደራል ፍርድ ቤቶች የችሎት ስርዓት ዓላማና ግብ

5. ዓላማ

የችሎት ስርዓት መመሪያ ዓላማ በህግ ለፍርድ ቤቶች የተሰጠ ስልጣንን በአግባቡ ለመተግበር እና ተገልጋዩም የችሎት ስርዓትን በመረዳት ለፍርድ ቤት እና ለችሎት ያለውን ክፍተኛ ስነምግባር በጠበቀ ተቋማዊ ባህልን መገንባት እና ማስከበር ነው።

6. ግብ

የችሎት ስርዓት መመሪያ ግቦች የሚከተሉት ናቸው፡-

1. የፍርድ ቤቶች እና ችሎቶች የሚመሩበትን ስርዓት መዘርጋት፣
2. በከፍተኛ ስነ ምግባር በመታነፅ ተቋማዊ ባህል መገንባት፣
3. ወጥነት እና ግልጽነት ያለው የችሎት ስርዓት እንዲኖር ማስቻል፣
4. የችሎት ስርዓትን ዳኞች፣ ተከራካሪ ወገኖች፣ የችሎቱን ሂደት ለመከታተል ችሎት ላይ የተገኙ ሰዎች እና ሌሎችም እንዲያውቁ እና እንዲመሩበት ማድረግ፣
5. የህብረተሰቡን አመኔታ ማረጋገጥ፣

## ክፍል ሶስት

## ቅድመ ችሎት ስርዓት

7. የቅድመ ችሎት ስርዓት

1. ችሎት ከመጀመሩ በፊት የችሎት ውሎ ፕሮግራምን የሚያመላክት እንዲሁም በእለቱ የተቀጠረ መዝገብ ቁጥር፣ የተቀጠረበት ሰዓት፣ የባለ ጉዳዮችን ስም፣ የጉዳዩን አይነት እና ጉዳዩ የተቀጠረበት ምክንያት የሚያመለክት በማስታወቂያ ሰሌዳ ወይም በቴሌቪዥን ማሳያ በግልጽ ቦታ መለጠፍ ወይም መዘጋጀት አለበት፡፡
2. የችሎቶች፣ የዳኛ ቢሮ፣ የሬጅስትራር ቢሮ፣ የመረጃ ዴስክ፣ የአስተዳደር ሰራተኞች ቢሮ ስያሜ በግልፅና ለባለጉዳዮች በሚታይ መልኩ በፅሁፍ መገለፅና በየበሩ መለጠፍ አለበት፡፡
3. ከችሎት መጀመር በፊት በተለይም የችሎት አገልግሎት ሐላፊዎች፣ ባለሞያዎች እንዲሁም ጉዳዩ የሚመለከታቸው የፍርድ ቤት ሰራተኞች ችሎቱ ስለመፅዳቱ ማረጋገጥ፣ በችሎት አዳራሽ መብራት፣ የእለቱ መዝገብ ፣የዳኛ አጀንዳ፣የዳኞች ስም ያለበት የጠረጴዛ ባጅ፣ ህጎች፣ የችሎት ወረቀት፣ ብዕር፣ የድምጽ መቅረጫ፣ ችሎት መዶሻ እንዲሁም በችሎት መሟላት ያለባቸው በሙሉ ስለመሰናዳታቸው መረጋገጥ አለበት፡፡
4. ለወንጀል ችሎት አቃቢያነ ህጎች፣ ጠበቆች፣ ባለ ጉዳዮች፣ በወንጀል የተጠረጠሩ ወይም የተከሰሱ ሰዎች እንዲሁም ሌሎች ሰዎች ችሎቱ ከመጀመሩ በፊት ወደ ችሎቱ አዳራሽ ወይም ክፍል ገብተው ከዳኛው ፊት ለፊት አቃቢያነ ህጎች ከችሎቱ በቀኝ በኩል፣ ተጠርጣሪዎች በስተግራ በኩል በተዘጋጀ ሳጥን፣ ተከሳካይ ጠበቃ በስተግራ በኩል ከተጠርጣሪ ጎን፣ ምስክሮች ከዳኞች ከሁለት ሜትር ርቀት በላይ በተዘጋጀ ማረፊያ፣ አስተርጓሚ ከምስክሩ ወይም ከሚያስተረጉመው ሰው አጠገብ፣ የችሎት ፀሀፊ ከችሎቱ ስቴጅ ፊት ለፊት በተዘጋጀ ቦታ እንዲሁም ታዳሚዎች በችሎቱ በተዘጋጀላቸው ቦታ ስፍራቸውን መያዝ አለባቸው፡፡

5. ለፍትሀብሔር ከሳሽ ከችሎቱ በቀኝ በኩል፣ ተከሳሽ በስተግራ በኩል በተዘጋጀ ቦታ፣ ጠበቃ በስተግራ ወይም በስተቀኝ ወክሎ በሚከራከረው ሰው ጎን ፣ ምስክሮች ከዳኞች ከሁለት ሜትር ርቀት በላይ በተዘጋጀ ማረፊያ፣ አስተርጓሚ ከምስክሩ ወይም ከሚስተረጉመው ሰው አጠገብ፣ የችሎት ፀሀፊ ከችሎቱ ስቴጅ ፊት ለፊት በተዘጋጀ ቦታ እንዲሁም ታዳሚዎች በችሎቱ በተዘጋጀላቸው ቦታ ስፍራቸውን መያዝ አለባቸው።

6. በዚህ አንቀጽ ከላይ የተደነገገው ስርዓት ከተፈጸመ በኋላ የችሎት ስርዓት አስከባሪው ወይም የችሎቱ ፖሊስ በችሎቱ አዳራሽ ውስጥ የተገኙትን ሰዎች በሙሉ ዳኞች ወደ ችሎት ሲገቡ ተነስተው እንዲቀበሏቸው በማሳሰብ ከዳኞች ፅህፈት ቤት በመሄድ ከእነርሱ ቀድመው ችሎት በማስገባት፣ የመቀመጫቸው ቦታ ሲደርሱ ለዳኞች የወታደራዊ የአክብሮት ሰላምታ በምልክት በመስጠት፣ ችሎት ውስጥ ወዳሉት ሰዎች በመዞር እነርሱንም በምልክት ሰላምታ ጠይቆ እንዲቀመጡ ማድረግ አለበት።

## ክፍል አራት

## የችሎት ስርዓት

8. የችሎት አጀማመር ስርዓትና ሰዓት

   1. የመንግስት መደበኛ የስራ ሰዓት እንደተጠበቀ ሆኖ የችሎት ስራ ጠዋት 3:30 እና ከሰዓት በ8:00 መጀመር አለበት።
   2. የአየር ሁኔታ ፀባይ በተለየ ሊታዩ የሚገባቸው እንደአካባቢው ነባራዊ ሁኔታ ሊቀያየር ይችላል።
   3. ዳኛው በችሎት መዶሻ በመምታት ችሎቱ ስለመጀመሩ ማብሰር አለበት።

9. ባለ ጉዳዮች የሚስተናግዱባቸው ቅደም ተከተል

   ዳኛው ጉዳዮችን በጉዳዮች ፍሰት አስተዳደር መመሪያ መሰረት በመቅጠር፣ ቅድሚያ ሊሰጣቸው የሚገቡ ጉዳዮችን ቅድሚያ በመስጠት እንዲሁም ባለጉዳዮችን በጉዳዮች ፍሰት አስተዳደር መመሪያ መሰረት ቅድሚያ በመስጠት ማስተናገድ አለበት።

10. የቃለ መሐላ ስርዓት

   1. ዳኛው ወይም የፍርድ ቤቱ አስተዳደር ሰራተኛ የቃለ መሀላውን ዓላማ እና ውጤት በማስረዳት አግባብነት ባላቸው የወንጀል እና የፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ህጎች ድንጋጌዎች መሰረት ቃለ መሀላ ማስፈፀም አለበት።
   2. ቃለ መሀላ ፍትህን እና እውነትን በማውጣት ረገድ ከፍተኛ ድርሻ ስላለው በህግ አግባብ የመማል ግዴታ ያለበት ማንኛውም ሰው፣ተከራካሪዎች፣ አስተርጓሚን ጨምሮ ለችሎት ለመናገር ሲገደድ በሚችል አግባብ መማል አለበት።

3. ቃለ መሀላ በዳኛ ፊት ሆኖ መሀላው በዳኛ ወይም በፍርድ ቤቱ አስተዳደር ሰራተኛ የሚፈጸም ሆኖ ቃለ መሀላው በግልፅ ለችሎቱ ሊሰማ በሚችል መልኩ በየተናጠል መፈፀም አለበት፡፡

11. ለችሎት ክብር ስለመቆም

1. በችሎት ሂደት ፍርድ፣ ቅጣት፣ ውሳኔ ወይም ብይን ሲነበብ፣ የክስ እና መልስ ቅብብል ሲደረግ፣ ክርክር ሲካሄድ፣ ባለጉዳዩ ምስክሮችን ሲያሰማ፣ ባለጉዳዩ አቤቱታ ሲያቀርብ፣ ትዕዛዝ ሲሰጥ፣ ውሳኔ ሲነበብ ወይም ዳኛው በያዘው ጉዳይ በሚያስችልበት ወቅት ጉዳዩ የሚመለከተው ባለጉዳይ ቆሞ መከታተል አለበት፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ስር የተደነገገው ቢኖርም ችሎቱ እንደየሁኔታው ክርክሩ የሚራዘም ከሆነ አንደኛው ወገን ሲናገር ሌላኛው ወገን እስከዚያ ድረስ እንዲቀመጥ፣ በጋራ ከተከሰሱት ወይም ከከሰሱት ሰዎች መካከል ምስክር ከሚያሰማ ወይም ከሚሰማበት ውጪ ያለው ተከሳሽ ወይም ከሳሽ እንዲቀመጥ እንዲሁም በህመም ወይም እርግዝና ወይም አካል ጉዳት ምክንያት መቆም የማይችል ሰው እንዲቀመጥ ዳኛው ሊፈቅድ ይችላል፡፡

12. ድምፅን ከፍ አድርጎ ስለመናገር

1. ዳኛ ችሎት ሲመራ ለችሎት ታዳሚዎች በሙሉ በሚሰማ መልኩ መናገር አለበት፡፡
2. ዓቃቢያነ ህጎች፣ ጠበቆች፣ ምስክሮች፣ ተከራካሪዎች እና ባለ ጉዳዮች ክርክራቸውን ሲያቀርቡ ዳኛው፣ ችሎቱ እና ተከራካሪው ወገን ሊሰማ በሚችል ሁኔታ መናገር አለባቸው፡፡

13. የአለባበስ ስርዓት

1. ማንኛውም ዳኛ ችሎት ሲያስችል የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ዳኛ በጥቁር ካባ መደብ ላይ ከአንገት እስከ እግር ጫፍ የሚደርስ ሰማያዊ ቀለም ያለው ካባ እና አንገት ላይ የሚታሰር ነጭ ሻሽ/ከረባት፣ ከአንገት የሚጀምር ወርቃማ መነሳነስ እንዲሁም በሁለቱም የካባው እጀታ ላይ ሶስት ሰማያዊ መስመሮች ያሉት፣

   የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ዳኛ ጥቁር ካባ መደብ ላይ ከአንገት እስከ እግር ጫፍ የሚደርስ ሰማያዊ ቀለም ያለው ካባ እና ከአንገት የሚጀምር ሁለት ወርቃማ መነሳነስ እንዲሁም በካባው እጀታ ላይ ሁለት ሰማያዊ መስመር ያለው ካባ፣

   የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ዳኛ በጥቁር ካባ መደብ ላይ ከአንገቱ እስከ እግር ሰማያዊ ቀለም ያለው ካባ እና ከአንገት የሚጀምር አንድ ወርቃማ መነሳነስ እንዲሁም በካባው እጀታ አንድ ሰማያዊ መስመር ያለው ካባ መልበስ አለበት፡፡

2. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1 የተጠቀሰው በወንጀል ነክ ነገር ውስጥ ገብተው የተገኙ ወጣቶች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡ ሆኖም የቤተሰብ፣ የሴቶችና የሕፃናት ችሎት ላይ ህፃናት በሚቀርቡባቸው ጉዳዮች ላይ ዳኞች፣ ተከራካሪዎች፣ የሕግ ባለሙያዎች እንዲሁም ችሎት አስከባሪዎች እንደ አስፈላጊነቱ በችሎት ካባ ሳያደርጉ ይችላሉ፡፡

3. የክልል ዐቃቢያነ ህጎች በተቋማቸው እውቅና ያለው ካባ በችሎት ለብሶ መገኘታቸው እንደተጠበቀ ሆኖ በችሎት የሚገኝ የፌደራል ዓቃቤ ህግ ሙሉ ጥቁር ካባ አንገቱ ላይ ቀይ የሆነ፣ ጠበቃ ሙሉ ጥቁር ካባ ነጭ ሪቫን፣ እና ተከሳካይ ጠበቃ ሙሉ ጥቁር ካባ አንገቱ ላይ አረንጓዴ የሆነ ለብሶ በችሎት መግባት አለበት፡፡ የካባው ዓይነትና ከለር ሲለወጥ ተቋሙ ለፍርድ ቤቱ ማሳወቅ አለበት፡፡

4. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1 እና 2 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም ዳኛ፣ ዓቃብያነ ህግ፣ ጠበቃ ከካባው ውስጥ ለወንድ ሙሉ ልብስ (ሱፍ/የጨርቅ) ኮትና ሱሪ፣ ሸሚዝ እና ከረባት እንዲሁም ለሴት ሙሉ ልብስ(ሱፍ/የጨርቅ) ኮትና ሱሪ ወይም ቀሚስ ፣ ሸሚዝ ወይም ሹራብ መልበስ እና ካባው እስከ አንገት ድረስ በቁልፍ ወይም በዚፕ የተዘጋ መሆን አለበት፡፡

5. ማንኛውም ነገረፈጅ ለወንድ ሙሉ ልብስ ኮትና ሱሪ፣ ሸሚዝ፣ ከረባት እንዲሁም ለሴት ሙሉ ልብስ (ሱፍ/ጨርቅ) ኮትና ሱሪ ወይም ቀሚስ፣ ከውስጥ ሸሚዝ ወይም ሹራብ መልበስ አለባቸው፡፡

6. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 4 እና 5 የተገለፀው እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም ዳኛ፣ የጉባኤ ተሿሚ፣ ዓቃብያነ ህግ፣ ጠበቃ ቁምጣ፣ ጅንስ፣ የተቀደደ ልብስ ፣ ቲሸርት፣ የተለያዩ ፅሁፎች ያለባቸውን አልባሳት፣ ሲሊፐር ወይም ሸበጥ ጫማ መልበስ የተከለከለ ነው፡፡

7. ማንኛውም ዳኛ፣ረዳት ዳኛ፣ ጠበቃ፣ ዐቃቢያነ ህግ ለወንድ በጣም የረዘመ፣ ድሬድ/ራስታ ፀጉር ፣ ለሴት እይታን የሚከለክል የፀጉር አሰራር እንዲሁም ኮፍያ ማድረግ የለበትም/የለባትም፡፡

8. የችሎት ፖሊስ ለዚህ ስርዓት የሚውል የደንብ ልብስ እንዲሁም የችሎት አስከባሪ መሆኑን የሚያሳይ መለያ መልበስ አለበት፡፡

9. ለሬጅስትራር፣ የችሎት ስነስርዓት አስከባሪ፣ ድምፅ ቀራጭ እንዲሁም በችሎ[illegible] ያለባቸው የፍርድ ቤቱ ሰራተኞች የችሎቱን ክብር የሚመጥን በፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በተዘጋጀ የደንብ ልብስ እና ጥቅማ ጥቅም መመሪያ መነሻ በፍ[illegible] ቤቱ ወጪ የተዘጋጀ የደንብ ልብስ ወይም ካባ መልበስ አለባቸው፡፡

Federal Supreme Court The Federal Democrtic Repbile of Ethiopia

10.የፍርድ ቤቱ አስተዳደር ሰራተኞች የተለየ የአለባበስ ስርዓት እንዲከተሉ አይገደዱም። ሆኖም በፍርድ ቤቱ የጥቅማጥቅምና የደንብ ልብስ መመሪያ የተፈቀደላቸው የፍርድ ቤቱ አስተዳደር ሰራተኞች በስራ ሰዓትና ቦታ የደንብ ልብስ የመልበስ ግዴታ አለባቸው።

11.በዚሁ አንቀፅ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ዳኞች፣ የጉባኤ ተሿሚዎች፣ ዓቃቢያነ ህግ፣ ጠበቆች፣ ፖሊስ እንዲሁም የፍርድ ቤቱ አስተዳደር ሰራተኞች የችሎቱን ወይም የፍርድ ቤቱን ክብር የሚያቀል ወይም የችሎቱን ስራ የሚያደናቅፍ ወይም የችሎቱን ክብር የማይመጥን በጣም አጫጭር የሆኑ ቀሚሶች፣ ሱሪዎች ቁምጣ ወይም ጥብቆዎች ለብሰው ችሎት መግባት የተከለከለ ነው።

12.የችሎት ታዳሚዎች እንዲሁም ተከራካሪዎች የወንጀል ድርጊትን የሚቀሰቅሱ ወይም በዳኝነት ሂደቱ ላይ ተጽዕኖ ሊያሳርፉ የሚችሉ ጽሁፎች ወይም መፈክሮች ያሉባቸውን ልብሶች ለብሰው ወይም በሰውነታቸው ላይ በመሳል ወይም በመነቀስ በችሎት እንዲታደሙ አይፈቀድም።

13.ማንኛውም ሰው በሐኪም ካልታዘዘለት በቀር አይኑ እንዳይታይ የሚያደርግ ወይም ጥቁር መነጽር አድርጎ ችሎት መግባት የለበትም።

14.ዳኛ፣ የጉባኤ ተሿሚ አቃብያነ ህግ ወይም ጠበቃ ማንነቱን ሊደብቅ የሚችል ኮፍያ ወይም ጥምጣም በጭንቅላት ላይ ጠምጥሞ ችሎት መግባት የለበትም።

15.ማንኛውም ሰው ፊት እና አይኑን ሙሉ ለሙሉ የሚሸፍን ወይም ሰው እንዳያየው የሚያደርግ ልብስ ለብሶ ችሎት መግባት የለበትም።

16.በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀፅ 14 እና 15 የተደነገገው ቢኖርም ዳኛ፣ የጉባኤ ተሿሚ፣ ጠበቃ እና ዐቃብያነ ህጎችን ጨምሮ በሐይማኖት ወይም በባህል ምክንያት የሚለበሱ ልብሶችን ለብሶ ችሎት መግባት ይቻላል። ሆኖም ችሎቱ የተከራካሪዎችን ወይም የችሎቱ ባለጉዳይን ማንነት ለማጣራት ወይም ለማረጋገጥ ሲል የዚያን ሰው ክብር፣ ባህል እና ሐይማኖት በማይጋፋ መልኩ ልብሱን ከላዩ ላይ እንዲያነሳ ማዘዝ ይችላል።

17.ማንኛውም ጠበቃ ወይም ዓቃቢያነ ህግ ከችሎት ውጪ ጋወን/ካባ በአግባቡ ለብሶ ወደ ችሎት መግባት አለበት፤ችሎት ላይ ጋዎን/ካባ ማውለቅ እና መቀያየር የለበትም።

18.ማንኛውም ሰው የፍርድ ቤቱን የጉባዔ ተሿሚ እና አስተዳደር ሰራተኛን ጨምሮ የችሎትን ፀጥታ በድምፅ የሚያውክ ድርጊት በችሎት ወይም በዳኞች ቢሮ/ፅ/ቤት [illegible] መፈፀም የለበትም።

19.የተጨማደደና ንጽሕናውን ያልጠበቀ ካባ ለብሶ ወደ ችሎት መግባት የተከለከለ ነው።

14. ተንቀሳቃሽ ስልኮች ወይም በድምጽ ሊያውኩ የሚችሉ ሌሎች ኤሌክትሮኒክስ መሣሪያዎች ማንኛውም የችሎት ታዳሚ ወይም ባለጉዳይ ተንቀሳቃሽ ስልኮችን ወይም በድምጽ ሊያውኩ የሚችሉ ሌሎች ኤሌክትሮኒክስ መሣሪያዎችን ወደ ችሎት ከመግባቱ በፊት ድምፅ እንዲያጠፋ ይገደዳል።

15. ችሎቱን ስለማክበር

ማንኛውም የፍርድ ቤቱ ሰራተኛ፣ፖሊስ፣ የችሎቱ ተገልጋይ፣ ተከራካሪ ወይም ባለጉዳይ በሚከተሉት ሁኔታዎች እራሱን ዝቅ በማድረግ ለችሎቱ ያለውን ክብር ሊያሳይ ይገባል፤

1. ዳኛው ችሎት ሲሰየም ችሎት አስችሉ ሲወጣ፣
2. ዳኛ ተሰይሞ ሳለ ወደ ችሎቱ ሲገባና ሲወጣ፣
3. ማንኛውም ባለጉዳይ በችሎቱ አቋም ባይስማማም ዳኛው ትዕዛዝ፣ ብይን፣ ፍርድና ውሳኔ አንብቦ ሲያጠናቅቅ፣
4. ዳኞችም ችሎት ሲሰየሙና ችሎት አጠናቀው ሲወጡ፣

16. የዳኞች መጠሪያ ስያሜ

1. የፍርድ ቤቱ መሪ እንዲሁም የበላይ አመራሩ በማንኛውም ወቅት እንደ ቅደም ተከተላቸው የክብር ስማቸውን ለሴት «ክብርት» ለወንድ «ክቡር» ኃላፊነታቸውና ሙሉ ስማቸው በመግለፅ እና ተገቢውን ክብር በመስጠት ንግግር ሊደረግ ይገባል።
2. ማንኛውም ሰው በችሎት ውስጥ ወይም ከችሎት ውጪ ማንኛውንም የፌደራል ፍርድ ቤት ዳኛን ሲጠራ ለሴት «ክብርት ዳኛ» እንዲሁም ለወንድ «ክቡር ዳኛ»፣ በማለት መጥራት አለበት።

17. በግልጽ ችሎት ስለመዳኘት

1. በዝግ ችሎት እንዲታዩ በህግ ከተደነገጉት ውጪ ማንኛውም ጉዳይ በግልጽ ችሎት መካሄድ አለበት።
2. ማንኛውም ሰው ችሎት ገብቶ የችሎቱን ሂደት የመከታተል መብት አለው። ሆኖም ችሎት ከሞላ እንደአመጣጡ፣ የተከራካሪ ቤተሰቦች እንዲሁም እየተካሄደ ባለው ክርክር ጉዳዩ የሚመለከተው በችሎት እንዲገባና እንዲከታተል መደረግ አለበት።

18. የቀጠሮ አሰጣጥ ስርዓት

1. ማንኛውም ዳኛ በፌደራል ፍርድ ቤቶች በጉዳዮች ፍሰት አስተዳደር መመ[illegible] ለጉዳዩ በተቀመጠው ጊዜ መሰረት መዛግብትን መቅጠር፣ ማስተናገድ[illegible] መስጠት አለበት።

2. ማንኛውም ዳኛ መዝገብ ሲቀጥር ጉዳዩ የሚታይበትን ሰዓት፣ ቀን እና ወር እንዲሁም ችሎት ለይቶ ማግለጽ አለበት።

3. መዝገቡ አልባት ካልተሰጠው ወይም ካልተቋጨ ወይም በህግ መሰረት ለጊዜው መዝገቡ ስለመዘጋቱ በግልፅ በመዝገብ ላይ ካልሰፈረ በስተቀር በመዝገቡ ላይ ቀጣዩ ሂደት፣ ሂደቱ የሚከናወንበትን ቀንና ጊዜ ዳኛው ለባለጉዳይ ማሳወቅና በመዝገቡ ላይ ማስፈር አለበት።

19. በችሎት የተከለከሉ ድርጊቶች

ማንኛውም ሰው በችሎቱ ላይ የሚከተሉትን ድርጊቶች መፈጸም ክልክል ነው፡-

1. ዳኛው በችሎት እያስቻለ ችሎቱን በሚያውክ ጎኑ ካለው ወይም ከሌላ ሰው ጋር ለሌላ ሰው በሚሰማ ድምፅን ከፍ አድርጎ ማውራት፣ መሳቅ፣ በተንቀሳቃሽ ስልክ መነጋገር፣
2. ድምፅ በሚያሰማ፣ እይታን በሚከለክልና የሌሎችን ሰዎች ትኩረት በሚስብ መልኩ ጋዜጣ እና ማንኛውንም ሌሎች ጽሁፎችን በችሎት ማንበብ፣
3. በድምጽ፣ በምልክት ወይም በማንኛውም ሁኔታ ችሎቱን ማወክ ወይም ለክርክሩ አስፈላጊ ያልሆነ ድርጊት መፈፀም፣
4. ከውሀ በስተቀር ሌሎች መጠጦችን መጠጣት፣ መመገብ፣ ጫት መቃም፣ ሲጋራ ማጨስ፣ ማስቲካ ማኘክ፣ መተኛት፣
5. የችሎት ታዳሚዎች በነፃነት የመቀመጥ መብታቸው እንደተጠበቀ ሆኖ ሌላ ሠው እንዳያልፍ በሚከለክል መልኩ እግርን ዘርግቶ መቀመጥ፣ በጠረጴዛ ላይ መቀመጥ፣ ሰው ወደ ችሎቱ እንዳያልፍ በተቀመጡ መከለያዎች ላይ መቀመጥ፣
6. ቃጠሎ የሚፈጥሩ መሳሪያዎችን ይዞ መግባት፣ የጦር መሳሪያ፣ ዱላ ወይም ስለታማ የሆኑ መሳሪያዎችን መያዝ ሆኖም የችሎቱን ስነ ስርዓት አስከባሪ፣ ተጠርጣሪውን ወይም ታሳሪውን ይዞ ወደ ችሎቱ የመጣውን ፖሊስ ወይም በልዩ ችግር ምርኩዝ ዱላ ይዞ የሚንቀሳቀስን አይጨምርም፣
7. ከፍርድ ቤቱ አመራር እና ከዳኛው ፍቃድ ሲሰጣቸው የመገናኛ ብዙሀን ብቻ ችሎቱን በድምፅ፣ በምስል መቅረፅ እንዲሁም ፎቶ ማንሳት እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም ሰው ችሎቱን በተንቀሳቃሽ ስልክ፣ በካሜራ ወይም በቪዲዮ ፎቶ ማንሳት፣ ምስል ወይም ድምጽ መቅዳት የተከለከለ ነው።
8. እንደ ሻንጣ እና ትላልቅ ቦርሳዎች ወይም ለችሎቱ ስነ-ስርዓት የማይመች ድምጽ መፍጠር የሚችሉ ማንኛውንም እቃዎች ይዞ ወደ ችሎቱ መግባት፣ በማንኛውም መልኩ የችሎቱን ሰላምና ፀጥታ ማወክ የተከለከለ ነው።

20. ከዳኞች የሚጠበቅ ስርዓት

1. የችሎቱን ስነ ስርዓት ማክበርና ማስከበር፣
2. የችሎቱ የእለት መዝገብ መዘጋጀቱ፣ ባለጉዳዮች መዘጋጀታቸውን ማረጋገጥ፣ መዛግብትን እንደተቀጠሩበት ቅደም ተከተል የተዘጋጁ መሆናቸውን ማረጋገጥ፣
3. የስራ ሰዓትን አክብሮ ችሎት መሰየምና መምራት፣ በበቂ ምክንያት ካረፈዱ ባለ ጉዳዮችን በማክበር ይቅርታ መጠየቅ፣
4. የችሎቱ ሰብሳቢ ዳኛ ወይም ዳኛ ጠረጴዛውን በችሎት መዶሻ በመምታት ችሎቱ ስለመጀመሩ ማብሰር፣
5. ለእለቱ ጉዳይ በቀረቡት መዛግብት ላይ በቂ ዝግጅት ማድረግ፣
6. ዳኛ ችሎቱን ሲመራ የህዝቡን ባህል፣ ወግ እና ሐይማኖት በማክበር መምራት፣
7. ለተከራካሪዎች ለፍርድ ቤቱ አስተዳደር ሰራተኞች፣ ፖሊሶች፣ ለተለያዩ መስሪያ ቤቶች ተወካዮች፣ የችሎት ታዳሚዎችን ወይም ለማንኛውም ተገልጋይና ባለጉዳይ ክብር መስጠት እንዲሁም የግራና ቀኝ ምስክሮችን መብታቸውን በማክበር እና በእኩልነት ማስተናገድ፣
8. ተከራካሪ ወገኖችን፣ ምስክሮችን እና ሌሎች ችሎቱን የሚከታተሉ ሰዎችን አክብሮት በሚያሳይ መልኩ የሙያ ማእረግ በመጠቀም፣አቶ ወይም ወ/ሮ፣ወ/ሪት ወይም እርስዎ በሚሉት ቃላት መጥራት፣
9. በቀጠሮ እለት ውሳኔ ወይም ትዕዛዝ ካልደረሰ ምክንያቱን ለባለ ጉዳዮች በመግለጽ ይህንኑ በመዝገብ ላይ በመመዝገብ ጉድለቱ የፍርድ ቤት ወይም የችሎቱ ወይም የዳኛው ከሆነ ይህንኑ ለባለ ጉዳዮች በመግለጽ በትህትና ይቅርታ መጠየቅ፣
10. ማንኛውም ዳኛ የዳኝነት ፍትሀዊ አካሄድ መርህ በተላበሰ ማንኛውም ባለጉዳይ ሳይሸማቀቅ ሀሳቡን በነጻነት እንዲገልፅ ማድረግ፣
11. ዳኞች ባለጉዳዮችን፣ ተከራካሪዎችን እንዲሁም ጉዳዮችን፣ ህጎችን፣ የዳኝነት ስነምግባር እና የዲስፕሊን ክስ አቀራረብ ደንብ እንዲሁም የጉዳዮች ፍሰት አስተዳደር መመሪያ ድንጋጌዎችን በጠበቀ መልኩ ማስተናገድ አለባቸው።

21. ከባለጉዳዮቹ የሚጠበቅ ስነምግባር

1. የችሎት ባለጉዳዮች የሚከተሉትን መተግበር አለባቸው፡-
   ሀ. በቀጠሮው ቀን፣ ቦታና ሰዓት መገኘት፣
   ለ. በችሎት በተዘጋጀላቸው ቦታ መቀመጥ፣
   ሐ. በቀጠሮ ቀን ለክርክሩ በአግባቡ ተዘጋጅቶ መቅረብ፣

መ. ሌላኛው ተከራካሪ በሌለበት ከዳኛ ፈቃድ ውጪ ወደ ዳኛ ቢሮ ያለመግባት፣

ሠ. ችሎት አስከባሪ ፖሊሶች፣ የችሎት አስከባሪ ሰራተኞች እንዲሁም ጠበቆች ስለ ችሎት ስርዓት ማወቅ እና ለባለጉዳዮች ማሳወቅ፣

ረ. ዳኞች በችሎቱ ሲኖሩም ሆነ በማይኖሩበት ጊዜ በችሎቱ ክፍል ወይም አዳራሽ ውስጥ የችሎቱን ስነ-ምግባር ለማስጠበቅ በችሎቱ የሚሰጠውን የማስከበሪያ ትዕዛዝ ማክበር፣

ሰ. የፍርድ ቤቱ ባለጉዳዮች የሚጠይቁትን ዳኝነት በህጉ አግባብ የፍርድ ቤቱን ሂደት እና አሰራር በማክበር መፈጸም፣

ሸ. ያቀረቡትን ክርክር፣ ተቃውሞ እና ሃሳብ በሙሉ በቀጥታ ወደ ፍርድ ቤት በአግባቡ ማቅረብ፣

ቀ. ማንኛውም ባለጉዳይ ክርክሩን ወይም ጉዳዩን ለዳኛ ሲያቀርብ ወይም ዳኛው ሲያናግረው ዳኛን ፊት ለፊት መመልከት፣

በ. በችሎቱ ላይ ተቃውሞውን፣ ክርክሩን እና ሁሉንም ሃሳብ ፍትህን፣ እውነታ እና አግባብነት ያላቸውን ማስረጃዎች ብቻ መሰረት በማድረግ ማቅረብ፣

ተ. በችሎቱ ክርክር ላይ የዳኛውን ስም መጥራት ሳያስፈልግ «የተከበረው ፍ/ቤት» ወይም «ክቡር ዳኛ» ወይም «ክብርት ዳኛ» በማለት መጥራት፤

ቸ. የችሎቱን ስነ-ምግባር የማረጋገጥ ግዴታ በቀደምትነት የዳኛው ድርሻ ቢሆንም የችሎቱ ስነ-ስርዓት እንዳይጣስ ማድረግ፣

ኀ. የችሎት ክብር የሚያቃልል ወይም የሚያውክ ካልሆነ በስተቀር ባለጉዳይ ወይም ተከራካሪ ሀሳቡን በማይገድብ ተገቢው አካላዊ እንቅስቃሴ በማድረግ መናገር፣

ነ. ባለጉዳዩ ችሎቱ ከመጀመሩ በፊት ምስክሮቹ መቅረባቸውን ማረጋገጥ፣

ኘ. በክሳቸው ወይም በመልሳቸው ላይ ከተዘረዘሩት ምስክሮች ጋር በሚጣጣም መልኩ ማንነታቸውን እና አድራሻቸውን (የመታወቂያ ወረቀታቸውን ይዘው እንዲቀርቡ በማድረግ) በአግባቡ በማረጋገጥ አጣምሮ ማቅረብ፤

አ. ማንኛውም በያዘው ጉዳይ ተከራካሪ የሆነ ሰው ምስክሮችን በአግባቡ ማናገር እና ክብራቸውን በመጠበቅ ጥያቄ ማቅረብ፤

ከ. ትዕዛዝ፣ ብይን ወይም ውሳኔ በሚነገርበት ጊዜ ወይም ዳኛ እየተ[illegible] የተቃውሞውን ቃል ሳያሳይ በስነ-ስርዓት እና በጸጥታ እስከመጨረሻው በመስማት ቅሬታ ያለው ከሆነ ጉዳዩ በሚመለከተው አካል ድጋፍ ወይም የችሎት ስርዓት በጠበቀ አቤቱታ ማቅረብ፣

Federal Supreme Court The Federal Democritic Repoblile of Ethiopian

ኸ. በመጠጥ ስካር ወይም በሱስ ተፅዕኖ ስር ሆኖ ወደ ችሎት መግባት ፈጽሞ የተከለከለ ነው።

ወ. ሳል ወይም ጉንፋን ያለው ባለጉዳይ ሁኔታውን ለችሎቱ በማሳወቅ በቅድሚያ እንዲስተናገድ መጠየቅ ወይም ከችሎት ውጭ ሆኖ ተራውን መጠበቅ፣

ዐ. ከአቅም በላይ በሆነ ጉዳይ፣ ህፃናት ልጆችን የያዙ፣ ነፍሰጡር፣ አካል ጉዳተኞች፣ አረጋውያን ችሎቱ በቅድሚያ እንዲያስተናግዳቸው ለችሎቱ በቅድሚያ ማሳወቅ አለባቸው።

2. ማንኛውም ባለጉዳይ የሚከተሉትን ተግባራት መፈፀም የተከለከለ ነው።

ሀ. በችሎቱ ዳኛ ክስ፣ ቅጣት፣ ውሳኔ ብይን ወይም ፍርድ መነበብ ወይም ምስክር መስማት ከተጀመረ በኃላ ማንኛውም ሰው ችሎት አቋርጦ መውጣት፣

ለ. ባለጉዳዩ ወይም ተከራካሪው ሀሳቡ እንዳይገደብ ማድረግ እንደተጠበቀ ሆኖ በችሎቱ ዳኛ በችሎቱ ላይ የተነገሩት ጉዳዮች ትክክል ስለመሆናቸው ወይም አለመሆናቸው በአይን ምልክት፣ በቅንድብ፣ በፊት ገፅታ ወይም በሌሎች ተገቢነት የሌላቸው ወይም አለመስማማትን በሚገልፅ አካላዊ እንቅስቃሴ ማሳየት ወይም ከዳኛው ወይም ከችሎት ዞር በማለት መናገር፣ ከዳኛ ጋር መሟገት ክልክል ነው፣

ሐ. በህክምና የተረጋገጠና በልዩ ሁኔታ በችሎቱ ዳኛ ካልተፈቀደ በስተቀር ማንኛውም የችሎት ባለጉዳይ የህግ ባለሙያዎችን ጨምሮ በችሎት አዳራሽ ውስጥ መመገብ ወይም ከውሀ ውጪ መጠጣት ወይም ማስቲካ ማኘክ፣

መ. በፍርድ ቤቱ ሲጋራ ለማጨስ ከተዘጋጀ ስፍራ ውጭ በማንኛውም ሁኔታ በፍርድ ቤቶች ችሎቶች እና አገልግሎት በሚሰጥባቸው ክፍሎች ውስጥ ማንኛውም ሰው ሲጋራ ማጨስ እንዲሁም በፍርድ ቤቱ ቅጥር ግቢ ጫት መቃም፣

ሠ. በፍርድ ቤቱ ቅጥር ግቢ፣ በችሎት፣ በዳኞች ጽ/ቤት አካባቢ ዳኞችን በድምጽ መረበሽ፣ ማወክ፣

ረ. ተከራካሪ ወገኖች ሳይፈቀድላቸው መናገር በክርክር ጣልቃ መግባት፣

ሰ. ዳኛ በሚናገርበት በማናቸውም ወቅት ጣልቃ በመግባት ማቋረጥ፣

ሸ. ለችሎቱ ጉዳያቸውን ሲያስረዱ ለአብዛኛው ህብረተሰብ ግልፅነት የሌላቸውን ቃላት ከመጠቀም መቆጠብ፣ በፍርድ ቤቱ የስራ ቋንቋ አቻ ቃላት ካጣ ችሎቱን ካላስፈቀደ በስተቀር ሌሎች ቋንቋዎች ቃላት መደባለቅ፣

ቀ. በማህበረሰቡ የተለየ ተገቢነት የሌለው ትርጓሜ በሚሰጥ ጣትን ወይም፣ ችሎቱ ባለጉዳይ ወይም ታዳሚ ላይ እየቀሰሩ ማውራት፣ ወይም ሀሳብን በ[illegible]

አካላዊ እንቅስቃሴ በመጠቀም መግለፅ እንደተጠበቀ ሆኖ እጅን ማወናጨፍና መሰል ተገቢነት የሌላቸውን አካላዊ እንቅስቃሴዎች እያደረጉ ማውራት፣

በ. ማንኛውም ተከራካሪ ክርክሩን ሲያቀርብ የሌላኛውን ወገን ሰብዕና ማዋረድ፣ ማስፈራራት፣ ማሸማቀቅ ወይም ማሸሟጠጥ፣

ተ. ተከራካሪ ወገኖች በችሎት ውስጥ በሚደረግ ክርክር ሃሳባቸውን በቀጥታ ለችሎቱ ከማቅረብ በቀር የጎንዮሽ ንግግር ማድረግ፣

ቸ. ከላይ የተዘረዘሩትና መሰል ተግባራትና የስነምግባር ጥሰቶች መፈፀም፣ ሕፃናት አስገዳጅ ሁኔታ ከሌለ እና የህፃናት ማቆያ ስፍራ በፍርድ ቤቱ ከሌለ በስተቀር ወደ ችሎት ይዞ መግባት የተከለከለ ነው።

## 22. ከሬጅስትራር፣ ከችሎት አገልግሎት እና ከፍ/ቤቱ አስተዳደር ሰራተኞች የሚጠበቅ ስነ-ምግባር

1. ለችሎቱ በቂ ድጋፍ የሚሰጡ የአስተዳደር ሰራተኞች መመደብና በማንኛውም ሁኔታ ሲጓደል ችሎት ከመጀመሩ በፊት ማሟላት፣
2. በእለቱ የተቀጠሩ መዛግብትን ከቀጠሮ ቀን በፊት ለዳኛ አሟልቶ ማቅረብ፣
3. የችሎቱን ስራ ሳያደናቅፉ ወይም ሳያውኩ መስራት፣
4. እርስ በእርስም ሆነ ባለጉዳዮችን በማክበር በአግባቡ ማስተናገድ፣
5. በዳኛው የሚሰጠውን ትዕዛዝ ማክበር፣ መቀበል እና በተገቢው ጊዜ በስራ ላይ ማዋል፣
6. ለችሎቱ ስራ እጅግ አስፈላጊ ካልሆነ በስተቀር ክርክር እየተካሄደ ዳኛውን፣ ተከራካሪ ወገኖችን፣ ምስክሮቹን ወይም ከማንኛውም ሰው ጋር አለማውራት፣
7. የፍ/ቤቱን መዝገብ እና ሰነዶች በአግባቡ መያዝ፣ በወቅቱ ለችሎቱ ማቅረብ ፣
8. ከችሎቱ ጋር በተያያዘ አስተዳደራዊ ጉዳዮች የሚመለከታቸው አስተዳደር ሰራተኞች ኃላፊነታቸውን ስለመወጣታቸው መከታተል፣
9. ለችሎቱ የሚያስፈልጉ ግብአት እንዲሟሉ መከታተልና እንዲሟላ ማድረግ፣
10. የመዝገቡን ሚስጥር መጠበቅ ማንኛውንም አይነት ማስረጃ ወይም ጽሁፍ ከችሎቱ ፍቃድ እና እውቅና ውጪ ከመዝገቡ ጋር እንደተያያዘ ማረጋገጥ፣
11. በዚህ መመሪያ የተገለፀው እንደተጠበቀ ሆኖ በጉባኤ ተሿሚዎች እና በአስተዳደር ሰራተኞች መተዳደሪያ ደንብ የተደነገጉ ኃላፊነትና ግዴታዎቻቸውን መፈፀም አለባቸው።

23. የቋንቋ አስተርጓሚ ኃላፊነትና ተግባራት

1. ቋንቋ የመተርጎም አገልግሎት በአግባቡ ማካሄድ፣
2. ባለጉዳዮችን ማክበር እና በአግባቡ ማስተናገድ፣
3. ያለአድልኦ ትክክለኛውን ትርጓሜ ማስተላለፍ፣
4. የዳኛውን ትዕዛዝ ማክበር፣ መቀበል እና መተግበር፣
5. በእውነት ለመተርጎም በገባው ቃለ መሀላ መሰረት መተርጎም፣
6. ሌሎች ፍርድ ቤቱ በሚያወጣው የአስተርጓሚዎች መመሪያ መሰረት የተገለፁትን ተግባራት መፈፀም አለበት፡፡

24. የችሎት አስከባሪ ሠራተኛ እና የችሎት ፖሊስ ኃላፊነትና ተግባራት

1. ማንኛውም ሰው የችሎት ስርዓት እንዲያከብር ማድረግ የችሎት ስርዓት ተጥሶ ሲገኝ ለችሎቱ ዳኛ የማሳወቅ፣
2. ዳኛን ሳይጨምር ወደ ችሎቱ የሚገቡትን ሰዎች በሙሉ በመፈተሽ ማስገባት፣
3. ዳኞች ወደ ችሎት ከመግባታቸው አስቀድሞ የችሎት ባለጉዳዮችን ችሎት ማስገባት፣
4. ችሎቱንና የዳኛውን/የዳኞችን ስም ለችሎቱ ታዳሚዎች መግለፅ እንዲሁም የችሎቱን ስርዓት ገለፃ ለችሎት ታዳሚዎች መስጠት፣ ስልክና ኤሌክትሮኒክስ መሳያዎች ድምፅ እንዲያጠፉ ማሳሰብ፣
5. ዳኛው የሚሰጠውን ትዕዛዝ ማክበር፣ መቀበል እና በአግባቡ መተግበር፣
6. ባለጉዳዮችን፣ ምስክሮችን፣ ተከራካሪ ወገኖችን እና ችሎቱን የሚከታተሉ ማናቸውንም ሰዎች ማክበር፣
7. የችሎቱ ክርክር በመካሄድ ላይ ሳለ በችሎቱ ካልታዘዘ በስተቀር ጣልቃ በመግባት መናገር ወይም በመንቀሳቀስ የችሎቱ ስራ እንዳይደናቀፍ ወይም እንዳይታወክ ማድረግ፣
8. ለችሎቱ ስራ እጅግ አስፈላጊ ካልሆነ በስተቀር ከዳኞች፣ ከምስክሮች፣ ከባለጉዳዩ እና ችሎቱን ከሚከታተሉ ከማንኛውም ሰዎች ጋር አለማውራት፣
9. ትዕዛዝ እና ውሳኔ በሚነበብበት ጊዜ በአግባቡ በመስማት እንዲተገበር የበኩላቸውን ድርሻ ማበርከት፣
10. ዳኞች ችሎት ሲሰየሙ እና ችሎት አጠናቀው ወደ ፅህፈት ቤት ሲሄዱ [illegible] ተገቢው ክብር እንዲያገኙ ማድረግ፣
11. ለዳኛው ሊቀርቡ የሚገቡ ሰነዶችን ዳኛው ሲፈቅድ ማቅረብ፣
12. የችሎቱን ፀጥታና ደህንነት ማረጋገጥ አለበት፡፡

Federal Supreme Court The Federal Democrtic Repoblile of Etiopian

25. የችሎት ደህንነትን ስለማስጠበቅ

1. ከዳኞች በቀር ማንኛውም ወደ ፍርድ ቤት ወይም ችሎት አዳራሽ የሚገባ ባለጉዳይ በደህንነት ፍተሻ ሥር የማለፍ ግዴታ አለበት።
2. ማንኛውም ወደ ችሎት የሚገባ ባለጉዳይ የህግ ባለሙያዎችን ጨምሮ ዱላ፣ ስለት ወይም የጦር መሣሪያ በመያዝ ወደ ችሎት ወይም ፍርድ ቤት ግቢ መግባት አይችልም።
3. ከላይ የተመለከተው ቢኖርም የፖሊስና ማረሚያ ቤት አባላት እስረኞችን ለማጀብ የተሰጣቸውን ሕጋዊ መሣሪያ እንደያዙ ፍርድ ቤት ግቢ መግባት አይከለከሉም። ሆኖም እነዚህን መሣሪያዎች ይዘው ወደ ችሎት አዳራሽ መግባት አይፈቀድላቸውም።

26. የችሎት ማጠናቀቂያ ስርዓት

1. ዳኛው ወይም ከአንድ ዳኛ በላይ የሆኑ ዳኞች የችሎት ስራውን ሲያጠናቅቁ ዳኛው ወይም የችሎት ሰብሳቢው ዳኛ በችሎት ውስጥ የተገኙትን ሰዎች በማመስገን ጠረጴዛውን በችሎት መዶሻ በመምታት ስለችሎቱ መጠናቀቅ ማሳወቅ አለበት፡
2. ችሎት ሲጠናቀቅ የችሎት ስርዓት አስከባሪው ወይም ፖሊስ ለዳኛው ወይም ለዳኞች የሰላምታ ምልክት በማሳየት ዳኞችን እና በችሎት ላይ የተገኙ ሰዎችን መሸኘት አለበት።

## ክፍል አምስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

27. ችሎቱ የሚወስዳቸው እርምጃዎች

1. የእርምጃ እና የቅጣት አላማ ሰው በፈጸመው ጥፋት ተፀፅቶ እራሱን ማስተካከል እንዲችል ማድረግ፣ ሌሎች ሰዎችም እንዲማሩበት ማድረግ እና የችሎቱ ክብር እንዲጠበቅ ማድረግ ነው፣
2. የችሎቱን ስነ ስርዓት በጣሰው በማንኛውም ሰው ላይ የችሎቱ ዳኛ የድርጊቱን አፈፃፀም እና ከተፈጸመው ጥፋት በስተጀርባ ያለውን ሃሳብ እንዲሁም ግለሰቡ በህግ ላይ ያለውን ግንዛቤ ከግምት በማስገባት ወዲያውኑ የሚከተሉትን እርምጃዎች መውሰድ ይችላል።
   ሀ. ማስጠንቀቂያ መስጠት፣
   ለ. ለተወሰነ ጊዜ ወደ ችሎቱ እንዳይገባ መከልከል፣
   ሐ. ከችሎቱ ክፍል እንዲወጣ ማድረግ ወይም

መ. በወንጀል በፍትሐብሔር እና አግባብነት ባለው ህግ መሰረት የቿሯቱን ስርዓት በመጣስ፣ በማወክ ወይም በማደናቀፍ ወንጀል ወዲያውኑ ፍርድ መስጠትና ቅጣት መወሰን አለበት።

3. የፍርድ ቤቱ አስተዳደር ሰራተኞችና የጉባዔ ተሿሚዎች መመሪያዉን ጥሰው ሲገኙ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 2 መሰረት ዳኛው የሚሰጠው ውሳኔ አስተዳደራዊ ተጠያቂነትን አያስቀርም።

28. የዳኛው ተጠያቂነት

1. ዳኛ ይህን መመሪያ የመፈፀምና የማስፈፀም ኃላፊነት አለበት።
2. ዳኛው የዚህን መመሪያ ድንጋጌዎች ከጣሰ በፌደራል ዳኞች የስነምግባርና የዲሲፕሊን ክስ ስነስርአት ደንብ ቁጥር 1/2013 መሰረት ተጠያቂ ይሆናል።

29. የፍርድ ቤቱ ተቋማዊ ኃላፊነት

ይህን መመሪያ የየፍርድ ቤቱ ተቋማዊ ኃላፊነትን በተመለከተ እንደፍርድ ቤቱ አቅምና የበጀት ሁኔታ ማሟላት የሚጠበቅበት ሆኖ፡-

1. ይህ መመሪያ ለህብረተሰቡ በመገናኛ ብዙሀን በቴሌቪዥን ዲስፕሌይ በፅሁፍ ማሳወቅና ግንዛቤ ማስጨበጥ አለበት።
2. ፍርድ ቤቱ የችሎት አዳራሾችን የሟሟላት ኃላፊነት አለበት።
3. የችሎቶችን ስያሜ የዳኞች ቢሮዎች የዳኝነት አገልግሎት መስጫ ክፍሎች በግልፅ ባለጉዳዮች እንዲያውቁት ማድረግ አለባቸው።
4. የመረጃ ዴስክ አገልግሎት እንዲጠናከር ማድረግ አለባቸው።
5. የጉዳዮች ፍሰት አስተዳደር መመሪያዎች ላይ የተገለፁ የተቋማዊ ኃላፊነቶችና ተግባራት መፈፀም አለበት።
6. ትልልቅ ንብረቶች፣ የጦር መሳሪያዎች የሚቀመጡበት የጥበቃ ቦታ ማዘጋጀት እንዲሁም አሰራር መዘርጋት አለባቸው።

30. መሸጋገሪያ ድንጋጌ

ይህ መመሪያ በፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት ከፀደቀ ከግንቦት 8/2014ዓ.ም በኃላ ጀምሮ በሚታተም ከ ሶስት ወር በኂላ ተፈፃሚ ይሆናል።

31. መመሪያውን ስለማሻሻል

የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ይህንን መመሪያ ሊያሻሽለው ይችላል።

የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት አስተዳደር ጽ/ቤት
Federal Supreme Court The ... Rep...

32. መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ በፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት ከፀደቀበት ከ ግንቦት 8 ቀን 2014 ዓ.ም ጀምሮ ከሶስት ወር በኋላ የፀና ይሆናል።

መዓዛ አሸናፊ

የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ፕሬዝዳንት